ለማድረግ የፖለቲካ ሃይሎችን የተጠናወቱት ከፍ ብሎ የተጠቀሱት ጠንቆች መሰናክል ናቸውና:: የኢትዮጵያ ህዝብ ሰላምን፣ ሰብአዊ መብቶንና ክብሩን፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶን፣ ፍትሃ ርትዕን፣ እኩልነትን፣ አርነትን፣ ... የሚፈልገው በየትም፣ ሁሉም ነው:: እስካሁን በተጓዝንባቸው መንገዶች እነዚህን የጋራ ፍላጎቶችን ልናሟላለት አልቻልንም:: ወደፊትም ባለንበት እየረገጥን የህዝቡን የሥቃይ ኑሮ ከምናራዝም ለኅብረት ትግል መሰናክል የሆኑትን ጠንቆች በውይይት በጋራ መድረኮች አፍረጥርጠን አውጥተንና በጥሞና መርምረን እናስተካክል:: የመጀመሪያው ርምጃም "ወይፍንከች የአባ ቢላዋ ልጅ/" ብለን የሙጥኝ የያዝናቸውን አንዳንዱ አመለካከቶች፣ አቋሞች፣ ፖሊሲያች፣ ስልቶች ዓላማዎች ከኢትዮጵያ ሠፊ ህዝብና ጭቁን ብሔሮች/ብሔረሰቦች የጋራ ፍላጎትና የኅብረት ትግል አንፃር መመርመርና ማስተካከል ሊሆን ይገባል:: አለዚያ "ቆመንልሃል፣ እናታግልሃለን፣ ..." የምንለውን ህዝብ በቀን ማግልገልና በትክክል መወከልና ለዱላም ማብቃት እንደተካኑን ይቆያሉ:: ታዲያ እስከመቼ ይዳከራል?

—ዲሞክራሲና ሠላም የተራዘመዉና የህብረት ትግል ውጤቶች ናቸው!

—እ ና ቸ ን ፋ ለ ን!!!